# እምዬ አፄ ምኒልክን መቃወም!
# በኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት ላይ ድፍረትና መነሳሳት ነው
# በዝምታ የሚታይ ጉዳይ አይሆንም !

ከቀመሩ ደሳለኝ

አፄ ምኒልክ ዘ፪ኛ ፣ የኢትዮጵያ አንድነት፣ገናና ታላቅነት፣የማይደፈር የኢትዮጵያ የነፃነት ታሪክ ስመ ጥሩ መስራች አባት ናቸው።በኢትዮጵያ ታሪክ ወደር የሌላቸው ጥበበኛ፣ብልህና ብልጥ መሪ፣ሕዝብን አፍቃሪ፣ ተንከባካቢ፣ሩኅሩህና አዛኝ፣ ደግና ቅን አሳቢ፣መልካም ተመኝና አርቆ ዓላሚ፣ ሰው አክባሪ የእውነት ሰው የነበሩና የተከበሩ ፣ ሕዝብም ለዚህ መልካም ባህሪና ተግባር **እምዬ ምኒልክ** በሚል ስም ከአጥናፍ እስከ አጥናፍ እከሌ ከእከሌ ሳይለይ የሚጠራቸው መሪ አባት፣ ጌታና የንጉሶች ንጉሥ ነበሩ፣ ናቸው።

ለነፃነት ፍቅራቸው፣ ለአገር አለኝታ ክብርና ኩራት፣ለሕዝብ ደህነትና ሰላም ከፍተኛ ጥበብ በተሞላበት ተጋድሎ ጠላት ወራሪ ፋሽስት ጣሊያንን አይቀጡ ቅጣት ቀጥቶና አሳፍሮ፣ አሽማቆ እንድመለ ያደረጉ ኢትዮጵያዊ ቀደምት መሪ ናቸው።የአውሮፖ የቅኝ ተስፋፊዎችንና ገዝዎችን የወረራ ዓላማ ቅስም የሰበረ፣ ተስፋ ያስቆረጠና የገታ፣ ለዓለም ኅብረተሰብ በተለይም ለአፍሪቃ የነፃነት ተስፋ ሰጭ የትግል ብርሃን ምዕራፍ አርአያን ያስተማሩ ሕዝባቸውን አንድ አርገው ያደራጁ፣አቅጣጫ የሰጡና የመሩ ዓለም ያደነቃቸውና የፈራቸው፣የኢትዮጵያ ሕዝብ ምንጊዜም የሚኮራባቸው ደፋር፣ብልጥና ጥበበኛ ጀግና አይበገሬ ኢትዮጵያዊነትን ለአገር ያጠነከሩ፣ ኢትዮጵያኒዝምን ለዓለም የትግል ተስፋ ያበረከቱ ብርቅዬ ጊዜ የማይሽረውና የማይፈታተነው ተግባን የፈጸሙ  የታሪካችን ምሰሶና ጉልላት አባት ናቸው።ለዚህም ትውልድ ሁሉ ለዘመናት በኩራት አርአያ  ያከብራቸዋል ይኖርባቸዋል ።

ለኢትዮጵያ ዘመናዊ የዕድገትና የእውቀት መነሻዎችን በጥልቀት ያስተወቁ፣ ከውጩ ዓለም ጋር ግንኙነትን የዲፕሎማቲክ ትስስርንና የንግድ ልውውጦችን በስፋት አቅደው ተግባራዊ ያደረጉ አንጋፋ ንጉሥ ናቸው። አፄ ምኒልክ ለኢትዮጵያ ወደር የሌለው ለውጥንና ዕድገትን፣ የሕዝቦችን መገናኘትና መቀራረብ፣ደህንነትና ሰላም፣ተስፋና ፍቅርን፣አንድነትና ኅብረተሰባዊ ኃይልና ኢትዮጵያዊነት ያጐናጸፉ ቅን አሳቢ የመልካም ምግባርና ሥነ_ሥርዓት፣የዲሲፕሊንና የመርሆ መሪ ጌታ አለቃ ነበሩ።ይህን የመሰለ ውብ መልካም ሥራ አከናውነውና አበርክተው አልፈዋል። ይህ ውብ ድንቅ ተግባራቸው በኛና በመጪው ትውልድ ሁሉ ለሕልውናችን መኖሪያና ተስፋ ሆኖ ለዘመናት የሚኖር ሕያው ታሪክ ነው።

ይህን ስመ ጥሩ ንጉሥና ታሪክ መዳፈር፣ በከንቱ ለማዛትና ግልብጥ ታሪክ በክህደት ማቅረብና ማውራት ከጠላት ፋሺስት ወራሪ ባህሪና ተግባር ተለይቶ አይታይም።በፋሺስት ጣሊያን ለምን አልተያዝንም አልተገዛንም  የባንዶች ቁጭት ባህሪ የሚያንጸባርቀው ነው።ኢትዮጵያዊነት የጐደለው የተዛባና የተጣመመ ውሸት፣ክህደት አዘል ራቁት ውሸት፣የሞተ ውሸት መሾረብና በፈጠራ ልብ ወለድ አጣሞና አንሻፎ ታሪክን ለማቅረብ መሞከር ከቅሌትም አልፎ አደገኛ የሰደድ እሳት ነው።

የእምዬ አፄ ምኒልክን ታሪክ ለማጉደፍና ለማራከስ የፈጠራና የውሸት ታሪክ ማተት፣ በወያኔ የክህደት ፕሮፓጋንዳ መመራትና በዚህ ውሸት ውስጥ ገብቶ መዳከር "ሞኝ የላኩትን አይረሳም" ዓይነት እንዳይገና አደጋና ችግር ላይ ከመውደቅ አስቀድሞ መጠንቀቁና ታሪክን ማወቁ መልካም በሆነ ነበር። ወያኔ/ሕውሓት የሰበከውን እንደ እውነት በመቀበል አገርና ታሪክን በቅጡ ያልተረዱ ሳያውቁ አወቅን ብለው ጥቂት የኦረሞ ተወላጅ ግብዞች ልባቸው ከጠባብ ጐጠኝነት ያልጸዳ፣ ያገር ፍቅራቸው ያደፈ፣ ከኢትዮጵያዊነት የራቁ ከሚያስቡት ክህደትና ውሸት የመጣ  የታሪክ ማዛባትና ማበላሸት ነው።ንጉሥ ምኒልክ የሚወቀሱ ሳይሆን የሚሞገሱና የሚከበሩ ሥራዎችን አከናውነው ተከብረውም ያለፉ መሪ ናቸው። እምዬ ምኒልክ የማንንም አካል ጡት እንዲጐዳ አላደረጉም አላስደረጉም።

መላው የኦረሞ ተወላጅ ሁሉ እምዬ ምኒልክን በመልካም ልቦናቸው የሚያቃቸውና የሚያከብራቸው እምዬ ምኒልክም ብሎ ያከበራቸው እንደሆነ ታሪክ ያመላክታል።ይህን የውሸት ፈጠራ ታሪክና የባለ ጥሩ ታሪክ መሪን ስም በመቃረን ለማዋረድና ለማጉደፍ የጡት ሃውልት ለማቆ የምትጥሩና ያቀዳችሁ የሌላው ክፍል ሕዝብ ብቻ ሳይሆን የኦረሞ ሕዝብ አይወድላችሁም፣አይቀበለውም።እንዳውም ይህን ከአግባብና ከሥነ_ምግባር ፣ከሞራልና ባህላዊ ይዘት የወጣ ትርጉም የለሽ፣ የውሸት ታሪክ በመቅረጽ የጡት ቅርጽ ማቆም ጸያፍና ነውር ነው።ሕዝብንም ማዋረድና መዳፈር  በሕዝብ ላይ እንደማሾፍና እንደማመጽ የሚቆጠር አሳፋሪ ተግባር ነው።

በውሸትና አሉባልታ ላይ ተመስርቶ የአንዲት የሴት ጡት አምሳል በእጅ ላይ ሃውልት ለመቅረጽና ለማቆም ማሰብ የንጉሡን ታሪክ አቃቁር፣ማጣጣል፣መቀልበስና ማጣመም የማይቻለውን መሞከር የማይተሰብ የማይሆን ቅዥት ነው ። መላ የኢትዮጵያ ሕዝብን ማስቀየምና ማስቆጣት ብዙ መጋፋትና መፈታተን ውጤቱ ጥሩ አይሆንም። በንጉሥ ምኒልክ እንዲሁም በአማራው ማኅበረሰብ ላይ የቅርብ ጊዜውን እንኳን ብናስብ ብዙ ግፍና እጅግ ዘግናኝ የማይረሱ ቁስሎች በኦረሞ እብሪተኞችና በወያኔ ዘረኞች ተፈጽመዋል። ይህ አልበቃ ብሎ ሌላ ማሰብና ታሪክን ለማዛባት ከመፍጨርጨር ቀድሞም የሰሩትን የጭካኔ በደል ማሰብና መታረም እጅግ ልባምነትና መፍትሄ ሰጭ በሆነ ነበር። በአማራው ላይ እንዲህ አምርሮ ማሴርና ማጥቃት፣መግፋትና ወደ ጥግ ማድረስ የከፋ ከመሆኑ ጋር ከጥግ ሲመለስ አደጋው ከባድ እንደሚሆን ይታሰብበት።የታሪካችንን ቁንጮ፣ የእድገትና የዘመናዊ ሥልጣኔ መሪያችንንማ ! ለመንቀፍ ማቀድና መነሳሳት ፈጽሞ የማይቻል፣ የማይሆን ነው።

ስለዚህ በዚህ ውሸት፣ፈጠራና የክህደት ታሪክ እቅድ የእምዬ አፄ ምኒልክን መልካም ታሪክ በመጻረን ቅጥ የለሽ የጡት ሃውልት በኢትዮጵያ የግዛት አንድነት ላይ ለማቆም ማሰብና አቅዶ መነሳት በኢትዮጵያና በኢትዮጵያዊነት ላይ መዳፋፈርና በጠላትነት አምጾ መነሳሳት የክህደት ወንጀል ነው።ይህ አሳብና ዓላማ፣ ታሪክን እንዲህ አቃሎ ማየት እጅግ ዝቅ ያለ አስተሳሰብ፣ ለራስ ደህንነት አለመረዳት ፣ለመጭው ትውልድና ለአገር አለማሰብ፣ ግብዝነት፣ ገለባና ትቢያ የሆነ የቀን ቅዠት ህልም ነው።ይህ በአንዳንድ እብሪተኛ ኦረሞች በወያኔ የተመከሩና የተደገፉ፣ አገራችን ኢትዮጵያን ወርሮ እየከፋፈለ ሕዝብን እያሰቃየ፣ ታሪክ እያጠፋና እያበላሸ በፀረ_ ኢትዮጵያ በማጥፋት ላይ ያለው የወያኔ/ኢህአዴግ ፈቃድና ተግባር ነው።

በመሆኑም የታሰበው ሃውልት አግባብነት የሌለው የኢትዮጵያንና ኢትዮጵያዊነትን፣ የመልካም ሥራ ቅርጽና ውበት የመሪያችንን ታሪክ፣የኛ ሁላችንን፣ ያለፈውን፣ ያለውንና የሚመጣውን ትውልድ ሁሉ የተጻረነ ፣የሚያጐድፍና የሚዳፈር ፀረ_ ኢትዮጵያ ስለሆነ እንቃወመዋለን፣ዝም ብለን የምናልፈውና የምናየውም አይሆን።እጅግ አደገኛ  መጥፎ የሃሰት ተልዕኮና የማይሆን አሳብ ይዛችሁ ከመጓዝ በአስቸኳይ ብታቆሙትና የተሰራውንም በማፍረስ የሕዝብ ንብረትን ከማባከን ባሻገር መልካም ከመሆኑ ጋር ከጥፋት ያድናል።

የእምዬ አፄ ምኒልክ ታሪክና አገረ ኢትዮጵያ አይደፈሩም፣አይገሰሱም።ምንጊዜም አክባሪና ጠባቂዎች አለን። ይህ ምክርና ማሳሰቢያ ነው።

**የእምዬ አፄ ምኒልክ ታሪክ ምንጊዜም ተከብሮ ይኖራል !**

**ምንጊዜም ኢትዮጵያ፣ኢትዮጵያዊነትና አረንጓዴ_ቢጫ_ቀይ ሰንደቅ ዓላማችን**

**ታሪክ ተዳፋሪ ጠላቶች ይወድማሉ ! !**